# የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ)

## Ethiopian People's Revolutionary Party (EPRP)

ነሐሴ 2 ቀን 2008 ዓ.ም.

**<u>የወያኔን ጸረ ሕዝብ ግድያ በጥብቅ እናወግዛለን፤ትግሉም ይቀጥል !</u>**

ትላንት እሁድ የባሕር ዳር ሕዝብ ያደረገውን ሰላማዊ ሰልፍ ለመበተንና በአጠቃላይም የተቀጣጠለውን የሕዝብ አመጽ እሳት ለማዳፈን ወያኔ በወሰደው የአፈና እርምጃ 30 ንጹህ ዜጎች ሲገደሉ ወደ 50 ቆስለው 60 ያህሉ ደግሞ ታግተዋል ። ይህ ወንጀል በጎንደር ሕዝብ ላይ እየተፈጸመ ባለው ግድያና በሌሎች ቦታዎችም በተፈጸመው አፈና ላይ የተጨመረ ነው ። አረመኔው ወያኔ ሰባት ሰዎች ሽብር ሊፈጽሙ ሲሉ ተገደሉ ብሎ ወንጀሉን ሊያቀልል መሞከሩም ተዘግቧል ። ከዚህ በተጨማሪ ባለፈው ቅዳሜና እሁድ አዲስ አበባን ጨምሮ በምዕራብ በደቡብና በምስራቅ ኢትዮጵያ በሚገኙ ከ200 በላይ በሆኑ ከተሞች በተደረገው የተቃውሞ ሰልፍ የወያኔ ጦር በወሰደው እርምጃ ከ50 በላይ ሰዎች መገደላቸውና በርካታ ሰዎች መታሰራቸው ተዘግቧል።

ኢሕአፓ ይህ የወያኔ አገዛዝን አረመኔያዊ ድርጊት በጽኑ እያወገዘ ይህ የተጀመረው የሞት ሽረት ትግል በተስፋፋና በተጠናከረ መልክ እንዲቀጥል ይጠራል፤ይጥራል ። የተጀመረው ትግልና እየተከፈለ ያለው መስዋዕትነት በድል መጠናቀቅ አለበት ። ድል ስንልም የወያኔ ውድቀት ማለታችን ነው ። ይህን ዘረኛና ጸረ ኢትዮጵያ አገዛዝ በተባበረ ትግላችን ማስወገድ ሀገራዊ ግዳጃችን ስለሆነ ይህ ቆራጥ ትግል ከግቡ ሳይደርስ መቆም የለበትም እንላለን ። ከወያኔ ሌላ ይህን የሕዝብ ትግል ለማደናቀፍ በራሳቸውም የተሳሳተ የፖለቲካ አቅዋም የተነሳ ይሁን ለባዕዳን አድረው ሆነ ጉዳት ሊያደርሱ የተነሱትን እኩይ ስምሪታቸውን እንዲተውናና በሕዝብ አንድነት ላይ ጋሬጣ መሆንን እንዲያቆሙ ያሳስባል ። የመረረው ሕዝብ ቆርጦና በቃኝ--እምቢኝ ብሎ ተነስቷልና ሊያቆመው የሚችል ምድራዊ ኃይል ሊኖር አይችልም ። በመሆኑም የወያኔ አፈናና ግድያ የሕዝብን ትግል የሚገታ ሊሆን አይችልም ። ወሳኙ ወቅት መጥቷልና ለወያኔ መሳሪያ ሆነው በሕዝብ ላይ ግድያና ወንጀል የሚፈጽሙት ሁሉ በጊዜ የጠመንጃቸውን አፈሙዝ ወደ ወያኔ ላይ እንዲያዞሩ ኢሕአፓ ያሳስባል ። አቅዋማቸውን ቀይረው ከሕዝብ ጎን የተሰለፉትንም እያደነቀ ሊሎችም የእነሱን አርአያነት እንዲቀበሉ ጥሪ ያደርጋል ። ይህ ትግል የኢትዮጵያዊነትን ኃይልና አቸናፊነት በግልጽ ያሳየ ነውና በሀገር ውስጥም በውጭም ያሉ ዜጎች ይህንኑ ተረድተው ትግል ከጀመሩት ጎን እንዲቆሙና ኢትዮጵያዊ ትግልን እንዲያጠናክሩ ጥሪ ያስተላላፋል ። ለሰማዕት ቤተሰብ ጽናቱን ይስጣችሁም ይላል--ለሀገር መሞት ክብር ነው ።
ታሪካዊው የሕዝብ ትግል ይቀጥል፤ይፋፋም። ዛሬም እንደ ትላንት ኢሕአፓ ከሕዝብ ጎን ተሰልፏል ።
አረመኔው የወያኔ አገዛዝ ይውደም!
ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ !!

**EPRP**
**P.O.BOX 73337**
**Washington DC, 20056**
**USA**

**Email ESPIC@aol.com**
**Website www.eprp.com**

**EPRP**
**BP 30022**
**92276 Bois Colombes cedex**
**France**

**Tel. 202 291 4217 Fax: 202 291 7645**